# የእነ መለስ ግፍና የኢትዮጵያዊው አማራ የዘር እልቂት

ማዕረግ ለሠይጣን አይሰጥም እንጂ ሳይንስን ተጠቅሞ ለሠራው ረቂቅ ክፋት ሊቀ-ሊቃውንት፣ ፕሮፌሰር፣ ዶክተር፣ ይህ ሁሉ ያንስበታል። ወታደራዊ ሹመት ለሠይጣን አይሰጥም እንጂ በግፈኞች ልብ ውስጥ አድሮ ያስፈጃቸው ሰዎች ብዛት ሲተመን ፊልድ ማርሻል፣ ጀነራል፣ ኮሎኔል ሲያንስበት ነው። አስተዳደራዊ ስያሜ ለሠይጣን አይሰጥም ሌዋታንን ተጠቅሞ ያፈናቀለው፣ ያስራበው፣ ያሳረደው፣ ሕጻናትና ሴቶች ቁጥር ሲቆጠር ንጉሥ፣ ፕሬዚዴንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሲያንስበት ነው። በእርግጥ ብዙዎች ከሠይጣን ባልተናነሰ እጅግ ክፋትና በደል ፈጽመው ፕሮፌሰር፣ ዶክተር፣ ፊልድ ማርሻል፣ ጄነራል፣ ፕሬዚደንት፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብለዋል። አንድን ዘር ሙሉ ለሙሉ ለመጨረስ የነደፈው እቅዱ ከሞላ ጎደል የሠመረለት ሂትለር ምን ዓይነት ምድራዊ ሹመት ሊሰጠው ይችላል?አማራን ስልታዊና ግልጽ በሆነ መንገድ ለማምከን፣ ለመግደልና ለማሰደድ አልፎ ተርፎም የኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ የሠይጣን ምልክት በመለጠፍ ሃሳቦቹ የሰመሩለት ለገሰ ዜናዊና ጓደኞቹ እነ ስብሃት ነጋስ ምን ዓይነት ምድራዊ ሹመት ይመጥናቸዋል?

ባይሎጂን፣ ኬሚስትሪና ፊዚክስን እየከፋፈሉ ለምርምርና ጥናት እንዲበቃ መንገዱን የጀመሩት የጥንት ፈላስፎች ናቸው። የነሱን ፈለግ ተከትለው ሊቃውንት ሳይንስን አሳድገው ለሕብረተሰቡ ጥቅም አዋሉት። የብሄር ጨቋኝ – ተጨቋን - ማህበራዊ ሳይንስ ፈልስፎ "አማራ ነው ጠላታችሁ" ብሎ ለጥቃት ያመቻቸው መለስ - ከግሪኩ የፈውስ መድሃኒት ተመራማሪ ጌለን (Galen) ይበልጥ ዓዕምሮውን አማራን ለማጥፋት ምርምር አውሎታል። ሊቃውንቱ ጌለንና ኢ-ሊቃውንቱ መለስ በምን ይተናነሳሉ። ጌለን ባዮሎጂን ለማሳደግ ወደላይ የሮጠውን ማይል ያህል መለስም ወደታች ሮጧል። ጌለን - anatomy, pathology, physiology, neurology - እያለ ምርምሩን በየፈርጁ ሲያስቀምጥ መለስም "ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ፣ እብሪተኛ፣ የድሮው ሥርዓት ናፋቂ" እያለ አማራውን በጠላትነት አስፈርጇል።

ኬሚስትሪ የተባለው ሳይንስ በንጥረ ነገሮች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት እያጠና ለህብረተሰቡ ጠቃሚ ነገሮች ይፈጥራሉ። Marie Curie, Louis Pasteur, Alfred Nobel, Thomas Graham እጅግ ታዋቂ የኬሚስትሪ ሳይንስ ግኝት ሊቃውንቶች ናቸው። መለስ ደግሞ አማራን ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በፍቅር የተዋሃደባቸውን ምስጢር አጥንቶ እንዴት ደግሞ መነጠል እንደሚችል ብሄርን ከብሄር የመነጠል ሳይንስን ያጠና አፍሪካ የጸነሰችው የዘመኑ ኢ-ሊቃውንት ነው። የኬሚስትሪው ሊቃውንቶች ወደ ላይ የሮጡትን ኪሎ ሜትር ያህል መለስም እንደ ሠይጣን ወደ ታች በመሮጥ ባባቱ ዲያብሎስ እግር ሥር ቁጭ ብሎ አማራን የማጥፋት የክፋትን ሃሳብ የተማረ ብኩን ነው። "አማራ ጠላታችሁ ነው አጥፉት" ሲል መለስ ለትግራዋዮች የጨለማ ትምህርት አስተምሮ እስከወድያኛው አሸለበ። በእድሜ ሳይሆን በዓዕምሮ

የመለስ የበኩር ልጅ የሆኑት ስብሃት ነጋ "አማራና ኦርቶዶክስ ላይነሱ ተቀብረዋል" ያሉት በመለስ የጨለማ ኬሚስትሪ ትምህርት ተመስጠው ነው። ቁሳካል አይፈጠርም፣ አይደመሰስም - ይህ ነው ሳይንሱ (matter can neither be created nor destroyed)። አማራም የፈጣሪ ቁሳካል ነው። ማንም አይፈጠረውም። አማራ ቁስካል ነው። ማንም አይደመስሰውም። መለስም ስብሃት ነጋም በጨለማው ትምህርት ተደናገሩ። እነሱ ተደናግረው ከርታታው በረከትን ካባ አልብሰው አማራን ያጠፋ ዘንድ ማርሻል፣ ሊቃውንት አድርገው ሾመው እሳቱ አማራ መሃል ሸጎጡት። የደብረ ማርቆስ አማራ በረከትን ያገኘ መስሎት ምድሩን ቀውጢ ያደረጉው ብርሃን (light)፣ ጊዜንና (time) ምህዳርን (space) አዋህዶ ነበር። በረከት ባለበት ቦታ በብርሃኑ ግለት ሞቷል። ዛሬ ምስሉ እንጂ በረከት አይደለም ሱሪ የለበሰው።

መለስ በፊዚክስም ቢሆን ከነ Albert Einestein, Stephen Hawking, Isaak Newton, Rene Descarts አይተናነስም። ፊዚክስ በቁሳካልና ኃይል (matter and energy) መሃል ያለውን ግኑኝነት ያጠናል። መለስም በአማራና በሌሎች ዘሮች መካከል ያለውን ንፅፅርና ዝምድና አጥንቷል። ፊዚክስ እንቅስቃሴን፣ ሙቀትንና ብርሃንን ያጠናል። መለስም ዝግመትን፣ ቅዝቃዜንና ጨለማን አጥንቷል። አማራን ከሌሎቹ ወንድምና እህቶቹ ዘር የነጠለው መለስ ከአባቱ ዲያብሎስ ጋር ወደ ጥልቁ ሮጦ ጨለማንና የጨለማውን ድቅድቅ ሥራ ካጠና በኋላ ነው።

አማራና ትግራይዋ ወንድምና እህቶቹ ልዩነት የላቸውም። መለስ ግን ወያኔን አየር በተሞላ ፊኛ (rubber ballon) ውስጥ ከቶ ከበላያቸው እንዲንሳፈፍ አደረገው። መለስ በዚህ ረገድ በ 1824 ዓም የላስቲክ ፊኛ ከፈጠረው ከሳይንስ ሊቃውንቱ - Michael Faraday - አይተናነስም። የትግራይዋ ሕዝብ ስለ ወንድሙና እህቱ የአማራ ሕዝብ ጥቃት አንዳች እንዳይተነፍስ መለስ በነጻነቱ ላይ ተረማምዷል ። ፊኛዋን ወደ ታች የማውረዱ ሥራ ቀላል ሳይንስ አይደለም። ይህን ሥራ ሊሠሩ የሚችሉት ፊኛዋ ውስጥ የታጎረውን አፍዝ አደንዝዝ የሙስናውን ሃይድሮጂን መቀነስ የሚችሉት ጥበበ የለበሱት የትግራይ ልጆች ብቻ ናቸው። የጨለማው ንጉሥ መለስ ቀላል ሰው አልነበረም። ጥሬ ሃብትን ዘርፎ፣ መብራትን እሙስናው ሠፈር ላይ ቦግ አድርጎ ደጋጉን የትግራይ ሕዝብ "የኤፈርት ሃብት ያንተ ነው" እያለ በጉጉት አማለለው። "ድንጋይ ዳቦ ነው" ብሎ የሚያሳምነው መልሰ እኮ በሥነ ዓዕምሮ ትምህርትም ቢሆን ከእውቁ - Sigmund Frewd – አይተናነስም። ጥቂር ሙስና የጋረደው አማኙ የትግራይ ሕዝብ ጨለማው ሲገፈፍለት ነገ ከወንድሞቹና እህቶቹ ጋር መቀላቀሉ አይቀርም።

መለስ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች መዲና የሆነችውን አዲስ አበባ የኦሮሞ ብቻ ነች የሚል ማወዛገብያና መከፋፈያ ሳይንስ አግኝቷል። አዲስ አበባ የሚኖረውን አብዛኛው አማራን ከኦሮሞች ጋር ለማቃረን ሲል "የሚኒሊክ ሠፋሪዎች" የሚል ስም አገኘ። ጥቂት ካድሬዎች ዛሬ "የሚኒልክ ሠፋሪዎች" የሚሉት መለስ በሙስና አነካክቶ ቢያንስ ባለ

ኮንዶሚኒየም ሲበዛ ደግሞ ባለ ኢንዱስትሪና ባለ ሕንጻ አልያም በውሸት ማስረጃ ለውጭ ሃገር ዜግነት ያበቃቸው ሰነፎች ናቸው። ሚኒልክ ሃገር ሲያስፋፉ አልገብርም ካሉት ጋር ሁሉ ተዋግተዋል። የጀግናው ካዎ ጦና የወላይታ ልጆች ይህን በበቀል አያነሱትም ምክንያቱም የመስፋፋት ጦርነት የነባራዊው ሁኔታ ማህበራዊ ፖለቲካዊ እውነታ መሆኑን ይገነዘባሉ። በጥበብ ያስተዳደሩት ሚኒልክ ከቅኝ ገዥዎች ባርነት ሕዝባቸውን የታደጉ ሰው ናቸው እንጂ እግዚአብሄር አይደሉም። ከሠፊ መልካም ነገሮች መካከል ትንሽቱን ስህተት አጉልቶ ሚኒልክን መናጀ በማድረግ "እንዲህ አደረጉ" እያሉ ማላዘን ሰዎችን የማታለያ ብሎም ሥልጣንን ለመጨበጥ፣ በሥልጣን አስታኮ ገንዘብና ኃብት ለመዝረፍ የሚደረግ ስልት (power seizur tactic) መሆኑን ታሪክንና በቅጡ የሚያውቁት የኦሮሞ ምሁራን ተናግረዋል። ሚኒልክን መናጀ የማድረጉ ሌላኛው ምሥጢር ደግሞ አማራ እንዳይደራጅ ለማዘናጋት ነው።

"የጉድ ቀን አይመሽም" እንዲሉ ዛሬ ደግሞ ማህበራዊ መገናኛው ምሁር ያደረጋቸው ጥቂት ሽሙንሙኖች "ሚኒልክ የኦሮሞዎችን ጡት የቆረጡ የኦሮም ጠላት ናቸው" የሚለውን የተስፋዬ ገብረአብን የጨለማ ትምህርት ተመርኩዘው "ሚኒልክ የኤርትራውያንን እጅና እግር የቆረጡ የኤርትራውያን ጠላት ናቸው፣ ቴዲ አፍሮ በሚልኒየም አዳራሽ ውስጥ የኃይለ ሥላሴንና ሚኒልክን ስም ማንሳት አልነበረበትም"የሚል ከንቱ ሃሳብ ያሰማሉ። ማንም እሺ አይላቸውም እንጂ – እነዚህ አሳሳቾች እንደ - አኖሌው ጡት - አስመራ መሃል -የቀኝ እጅና የግራ እግር - ሃውልት ቢቀረጽ ደስ ይላቸዋል። ለቅኝ ገዥዋ ኢጣልያ በክህደት የተሰለፉ ሁሉ በዘመኑ ህግ ነው ቅጣታቸውን ያገኙት። በዚህም ዘመን በአሜሪካም ይሁን ሩስያ – በጀርመንም ይሁን ታላቋ ብሪታንታ በክዳት ከጠላቱ ጋር የተሰለፈ ሁሉ በተደነገገው ህግ መሠረት ይቀጣል። በግፍ ላይ ግፍ የተፈራረቀበትን አማራን ይበልጥ ለማስጠላት የሚፈበረከው መላ ጎጅ ነው። ገና ለገና ከሙስናው ለመቋደስ ተስፋን የሰነቁ አንዳንድ የውሸት ፖለቲካ ቁማርተኞች እንዲህ አይነቱን ክፋት ሲዘይዱ ሊያፍሩ ይገባል። ዛሬ ሕዝቡ፣ ቂሮም ሆነ ፋኖ የተደበቀችውን የውስጥ ፍላጎትን ፈልፍሎ ያወጣል። ትላንት ህ.ወ.ሃ.ት. በግፍ ያባረራቸው ኤርትራውያኖች እንባ ሳይደርቅ በጨለማ ሃሳብ መዳከር ሌላ ጥፋት ያስከትላል። የሁሉም ነገር መፍትሄ እውነት ብቻ ነች። የፖለቲካ ብልጣብልጦች ጀግናውን ዘርዓይ ደርሰ ልብ ሊሉ ይገባል። ጨለምተኛ ስልት የትም አያደርስም። የኤርትራና ኢትዮጵያ ሕዝብ ትብብር ተፈጥሯዊና ዘላለማዊ ነው።

አማራ ያልተሠራበት ግፍ የለም። በሃያ ሰባት ዓመት ድፍን ዓመታት አማራን ቤተ ሙከራ አድርጎ መለስና ስብሃት አምክነውታል፣ ገድለውታል፣ አፈናቅለውታል፣ አሰድደውታል፣ አስልበውታል። አማራ ኢትዮጵያዊ ነው። አማራ እንደ ሌሎቹ ብሔርና ብሔረሰቦች እሱም ለሃገሩ ተሰውቷል። ታድያ አማራ ምን አድርጎ ነው መለስ ዜናዊ ይህን ያህል ግፍ የፈጸመበት? ኢጣልያ ደስ እንዲለው - ወይንስ ካለከልካይ ኢትዮጵያን ለዝርፊያና ሙስና ለማዘጋጀት? አማራ በመወለድ እትብቱን በመሞቱ ደግሞ አካሉን

አዋህዶ ኢትዮጵያን ይወዳታል። አማራ ሃገሩ ኢትዮጵያን ሌሎች እንዲነኩበትና እንዲዘርፏት አይሻም። ክርስትያኑም እስላሙም አማራ ለኢትዮጵያ ሲል አይተኛም። አማራ ኢትዮጵያዊነቱንና እምነቱን አንገቱ ላይ በማንተም አስሯል። ይህ ትውፊቱ ነው በነመለስ ያስወገዘው። በጀግናው አጼ ሚኒልክ በተመራው የአድዋ ጦርነት ሁሉም ብሔሮች ተሰልፈዋል። አማራ ድሉ የኔ ብቻ ነው አላለም። ይሁንና ግን አማራው እንደ አቶ ዜናዊ ዓይነቶቹን ባንዳ ባለማሰለፉ ምክንያት ኢጣልያ ከአርባ አመት በኋላ በቀልን አዝላ ዳግም ስትመጣ ሃያ አምስት ሺህ ቤተ ክርስትያኖችን አቃጥላ በርካታ የጎንደር፣ ወሎና ሰሜን ሸዋ አማራዎችን በስቅላት ገደለች። በበላይ ዘለቀ የተመራው የጎጃም አርበኛ ኢጣልያን በአካባቢው ድርሽ ስላላደረገ ምናልባት ይህ ቅጣት አልደረሰበት ይሆናል። የባንዳ ልጆች የአማራን ጥላቻ የተማሩት ከኢጣልያ ነው። መለስ ዜናዊ በትምህርቱ ባይገፋም እንኳን በትንሽ እውቀቱ ባዮሎጂን፣ ኬሚስትሪን፣ ፊዚክስንና ሳይኮሎጂን አማራንና ኦርቶዶክስን ለማጥፋት ተጠቅሞበታል። መለስ ዜናዊ በትምህርቱ ቢገፋ ኖሮ እንደ ጨለምተኛነቱ ከሆነ ኢትዮጵያንና ኤርትራን ብቻ አይደለም መላው አፍሪካን በጎዳ ነበር። ለዚህ ነው እኮ የአየር ንብረት በማስጠበቅ ሰበብ ምዕራብያኖቹ በሰጡት ስልጣን ተንጠላጥሎ በአፍሪካ ጉዳይ ዘው ሲል የነበረው። የኋላ ኋላ አስደነገጡት እንጂ (Meles: an extraordinary personality on environment and development) እያሉ እያሞካሹ አብሯቸው ፎቶግራፍ እንዲነሳ አድርገዋል። እነሱ ያላታለሉት ሃገር ወዳዶቹን ሚኒልክንና ጣይቱን ነው።

አማራ ጽኑ ኢትዮጵያዊ ነው፣ ሌላ ምክንያት የለውም - ዘሩን ከጥፋትና ከእልቂት (genocide) ለመጠበቅ ሲል ነው መደራጀቱና መተባበሩ። የአማራ ጠላቶች ዛሬም አልተኙም፣ ይልቁንም በርካታ ስልቶችን ሲነድፉ ይስተዋላል። "መደመሩን" ተከትለው ከውጭ የገቡ የአማራ ጠላቶችን ልብ በል! በየጊዜው በየምክንያቱ የሚፈናቀሉትን አማራ ልብ በል! በሶማልያ ክልል፣ በወለጋ፣ አርሲና በባሌ አካባቢ ያለውን አለመረጋጋት ልብ በል! እነመለስ አስቀድመው የአማራውን ነዋሪ ቁጥር ለማሳነስ በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ናዝሬትና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች ኦሮምኛ ተናጋሪ ሰዎች የማስፈራቸውን ምስጢር ልብ በል! ሱዳን ሆን ብሎ በአማራው ላይ የከፈተውን ጥቃት ልብ በል! አማራን ትጥቅ የማስፈታቱን ደባ ልብ በል! የኢንጂነር ስመኘው በቀለን ድንገተኛ ግድያ ልብ በል!ስለሆነም በመላ ኢትዮጵያ የሚገኝ በሚኒልክ ሠፋሪነት የተፈረጀው አማራ ጊዜ ሳያጠፋ በአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ውስጥ ሊደራጅ ይገባል። መላው የአጼ ፋሲልና አጼ ቴዎድሮስ ሃገር በጌምድር፣ ወልቃይጥ ጠገዴ፣ ጎንደርና ሌሎቹም – መላው የንጉሥ ተክለ ኃይማኖት ጎጃም፣ መተከል፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝና ሌሎቹም፣ መላው የዛግዌ ነገስታ ሃገር፣ የአጼ ላሊበላና ንጉሥ ሚካኤል ወሎ፣ ቤተ አማራ በሞላ – መላው የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ፣ ኃይለ መለኮትና አጼ ሚኒልክ ሰሜን ሸዋ፣ በደብረ ብርሃን፤ መንዝ፣ አንኮበር፣ ጅሩ፣ ተጉለት፣ ቡልጋ፣ ይፋት፣ መርሃቤቴ፣ መሬ፣ ሞጣ፣ ወገራ፣ እንሳሮ፣ ሸዋ ሮቢትና

በሌሎች አካባቢ፣ ያለህ አማራ ንቃ። የሸዋ አማራና የሸዋ ኦሮም ዝንተ ዓለም አብሮ በመኖረ ትብብርና መግባባቱ ዘላለማዊ ነው።

አማራ ጻድቅ ከጀግና ንጉሥ የሚፈልቅበት እንጂ የነመለስ ሜራ አንገቱን የሚያስደፋው አይደለም። አማራ "አትንኩኝ ከልክ አትለፉ"ይላል እንጂ ሌላውን አይጠላም። አማራ ለውደደው ማር ለጠላቱ እሬት ነው። አማራ የደረሰበት ግፍና መከራ እንዲደራጅ አስገደደው እንጂ ብሔርን ያማከለ ድርጅት ከቶም አይሻም ነበር። የደጋጉና አገር ወድዱ አማራ መደረጀት የእነ መለስና ጓደኞቹ ጨለምተኛ ሳይንስ ግፍ የወለደው ዘሩን ከዕልቂት የመጠበቅ ግዴታ ነው። አማራ የእስከ አሁኑ ጥቃት ይበቃዋል። አማራ እስከ መቼ ልጅህ ብልቱ ይሰለባል — እስከ መቼ በቀትር ጸሃይ ሕጻናትህ ይገደላሉ - እስከ መቼ ሱዳን ለም መሬትህን ይቀማል — እስከ መቼ ጉበትና ኩላሊትህ በአረመኔዎች ይበላል፣ እስከመቼ ትፈናቀላለህ - ። አማራ እራስህን አድነህ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትንም አፅና። አማራ ተደራጅ፣ ተባበር። እውቀትህን፣ ገንዘብህንና ጉልበትህን ራስህን ለማዳን አውለው። ጥቂት ቀን ነች፣ ሁሉም ያልፋል።

ኢትዮጵያ ለዘላልም ትኑር።